# ወገን ለኔ ብለህ ስማ!

በ ሀገራችን በኢትዮጵያ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በተለያየ ግዜ የሚነሱ መንግስታት በሚያራምዱት የፖለቲካ ፖሊሲ የተነሳ ይህም በፈጠረው ስራ አጥነትና እጅግ የከበደው የኑሮ ውድነት ዜጎች በገዛ ሀገራቸው ክልል እንደልባቸው ተንቀሳቅሰው መስራት ካለመቻላቸው የተነሳ በተወለዱበት ምድር መኖርና መስራት የማይቻልብት ደረጃ ስለተደረሰ በተገኘው አጋጣሚእና በገኙት አቅጣጫ ትውልድ ሀገራቸውን ለቆ የመሰደዱ ነገር እንደመፍትሄ ከተወሰደ አራት አስርት አመታት አስቆጠረዋል።
በተለያዩ የዜና አውታሮች እንሚገለጸው ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ያለገደብ ወደ ጎረቤት ሀገር በተለም ሱዳን ሊቢያና የመን የሚሰደደው ዜጋ ቁጠር እጅግ አሳሳቢ እየሆነ መጥ
ቷል።
በተለይም ከስደተኛው ቁጥር መብዛት ተከትሎ አሳሳቢ የሆነው ነገር በህገ ወጥ ደላሎች አማካይነት ይደረግ የነበረው ኢሰባዊ ድርጊት ከመበራከቱም አልፎ ወደ ተደራጀ የወንጀለኞችና አፋኝ ወንበዴዎች በማደጉ ስደተኞችን በማታለል ይደረግ የነበረው ህገ ወጥ ዝውውር በመሳሪያ ወደተደገፈ አፈና መሸጋገሩ ጥንት ከነበረው የባሪያ ስርዓት በጨከነ ሁኔታ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ሰደተኞች በአደባባይ ለገበያ የመቅረባቸው ጉዳይ ነው።

ነገሩ እንዲህ ነው በሱዳንና በግብፅ ድንበር ላይ የሚኖሩት ራይሻይዳ( ቀይ አረቦች) በሱዳን የሚገኘውን የስደተኞች ካምፕ በድንገት ጥሶ በመግባት በጦር መሳሪያ አስገድደው ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን በማፈን ወደ ሚሊና በረሀ ውስጥ በመሰውር ከተለያየ ቦታ ከፈኑዋቸው ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ጋራ በመጨመር ወደ ግብጽ ደንበር በስውር በማስጠጋት በዚህ ስራ ለተሰማሩ ግብጻውያን ሽፍቶች ጋር በመደራደር ይሸጧቸዋል።
ግብጻውያን ሽፍቶም በድብቅ ወደ እስራኤል ድንበር አቅራቢያ በሚገኘው ሲና በርሀ በመውሰድ በተለያየ ዋሻ ውስጥ ያስቀምጧችዋል።
ከዚህ በዋላ ነው እንግዲ በዜጎቻችን ላይ ከፍተኛ ሲቃይና እንግልት የሚደርሰው:- በመቀጠል የሙባይል ስልክ በመስጠት ወደ አሜሪካና ወደተለያዩ ሀገሮች ወደሚኖሩ ዘመዶቻቸው እንዲደውሉ በማደረግ ሰላሳ ሶስት ሺህ የ አሜሪካን ዶላር (33000) $ እነዲከፍሉ በማስገደድ ካልከፈሉ ግን እንደሚገድሉዋቸው ይናገራሉ። የገነዘቡ በጠን ብዙ ከመሆን ለመከፍል በጣም አዳጋች ቢሆንም መከፍል የቻሉ እስረኞች አንግኩዋን አይለቀቁም። ዘመድ የሌላቸውና መከፍል ያልቻሉትንም:-

1. ከፍተኛ ድብደባ ደርሶባቸዋል

Medina Menewera (New Maadi)
Bank El-Ahly Street Building No. 6/3
Cairo, Egypt
Tel 20 251 505 17
Gmail ercie2011@gmail.com
Ethiopian Refugee

2. በኤልክትሪክ ሳይቀር እያስያዙ ነፍሳቸውን እስኪስቱ ድረስ ያስቃይዋቸዋል
3. ሻማ እያቀለጡ መቀመጫቸውን በመፍሰስ ያሰቃይዋቸዋል
4. በቀለጠ ጎማ ጀርባቸውን አቃጥውታል
5. እግራቸው ለረጅም ግዜ በካቴና ታስረዋል
6. ውሀ በሚጠማቸው ግዜ ,ጋዝ እየቀላቀሉ ይሰዋቸዋል
7. በእርሃብና በ ውሀ ጥም ተሰቃይተዋል
8. በ 24 ሰዓት ውስጥ ለ2 ሰዓት ብቻ በእግራቸው ተቀምጠው ይተኛሉ
9. ከዚም አልፎ እነርሱን ለማስፈራራት ሲባል ሌሎችን እፊታቸው በጥይት እራሳቸውን ይበትኑታል

ከዚህ በዋላ በብዙ ስቃይና መከራ የከረሙት እስረኞች ገንዘብ ማምጣት ያልቻሉትን እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ ለዚሁ ስራ የተሰማሩ የእክምና ባለሙያዎችን በማስመጣት ኩላሊታቸውን በማውጣት የሚሸጥ ሲሆን ከዚህም መከራ አምልጠው ፖሊስ የታደጋቸው በበርሀ በሚገኙት በግብፅ እስር ቤቶች ይወረወራሉ ያለጠያቂ ከነ ቁስላቸው ከነ ህመማቸው ለብዙ ወራት የሚሰቃዩ ሲሆን በምግብና በህክምና እጦት ብዞዎቹ ይሞታሉ።

ከሞትም የተረፉትም ካይሮ በሚገኘው አናተር ወህኒ ቤት የሚያመጣቸዋል በዚሁ እስር ቤትም የሚታሰሩት አደገኛ ወንጀለኞች እና እድሜ ልክ የተፈረደባቸው ናቸው ኢትዮጵያውያን እስረኞቹም በእስረኞቹ ብዙ ስቃይ የሚደርስባቸው ሲሆን ይደበደባሉ ብሎብ ይደፈራሉ ሞተውም አስከሬናቸው የወጣም አሉ ። እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን እነዚህ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸውም ሆነ በግብጽ ምንም አይነት የወንጅል እሪከርድ ሳይኖርባቸው ሚደርስባቸው ግፍ ነው።

የሀገሪቱ ምንግስትም ለነዚህ ስደተኞቸች የሚሰጣቸው እድል ወደ ሀገራቸው እንዲሚለሱ ብቻ ሲሆን የ ስደተኞችን ጉዳይ ለመመልከት እድል ያለው UNHCR (ዩ ኤን ኤች ሲአር) የነዚህ ስደተኞችን ጉዳይ በስነስርዓት ካለመመልከቱም በላይ በነእርሱ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመስጠት እስከ አራት ዓመት ይፈጅባታል ይህም አልበቃ ብሎ አብዛኛውን የኢትዮጵያ ስደተኞችን ፋይል ዘግቻለሁ በማለት ወደ ሀገር እንዲመለሱ ውሳኔ ይሰጣል። ሀገራቸውን ጥለው እንደወጡ ያደረጋቸው መንግስትና ስርዓት ሳይቀየር መመለስ በጨንቃቸው በእስር ቤትውስጥ መቆየትን ይመርጣሉ በዚህም ምክንያት ብዙ ኢትዮጳያውያንና ኤርትራውያን እስረኞች ያሉ ሲሆን አሁንም ድረስ አምስት አመት ያስቆጠሩ እስረኞች በእስር ቤት ውስጥ አሉ። በወንዶች ላይ እንዲህ ከደረሰ በሴቶች ላይ ምን ሊደርስ እንደሚችል መገመት አይከብድም። አብዛኞቹ ሴቶች በጅምላ ከመደፈራቸው የተነሳ ያለማቋረጥ ደም ይፈሳቸዋል ለ ኤች አይ ቪ እና ለተለያዩ የአባላዘር ብሽታዎች የተጋለጡ ከመሆኑም በላይ ብዙዎቹ እርግዘው እዚያው እስር ቤት ውስጥ የሚወልዱበት አጋጣሚ አለ የተወለዱትም ህፃናት ቢሆኑም በምግብና በመድሀኒት ችግር በእርስር ቤት እንዳሉ ያልቃሉ።

በአሁኑ ሰዓት ከነዚህ ወንበዴዎች እጅ አምልጠው የመጡት አስራ ሰባት ስደተኞች ካይሮ በሚገኘው የ ኢትዮጵያ ስደተኞች ፅ/ቤት ከለላ አግኝተው አሉ።

ለግንዛቤ ያህል በነርሱ ላይም ከላይ የተጠቀሰው መከራ ሙሉ ለሙሉ የደረሰባቸው ሲሆን ሁሉም በራይሻይዳዎች በጦር መሳሪያ ታፍነው ከሸገራ የስደተኞች ከምፕ የተወሰዱ ሲሆን በቤተክርስትያን አገልግሎት ላይ የነበሩ ዲያቆናት ሳይቀሩ ታፍነው ወደ በርሃ ተሸጠዋል። ከነዚህም መሀል ከሱዳን ያስነሱዋቸው በቁጥር ሰላሳ ስድስት (36) ሲሆኑ በተለይ፡-



Medina Menewera (New Maadi)
Bank El-Ahly Street Building No. 6/3
Cairo, Egypt
Tel 20 251 505 17
Gmail ercie2011@gmail.com
Ethiopian Refugee

1 ሴቶቹ በበርሃው ውስጥ አልቀዋል
2 ሌሎቹም እናመልጣለን ሲሉ ተገድለዋል።
3 ከ ሁሉም በላይ እነዚህ ልጆች በሀዘን ተሰብረው የሚያነሱዋት የሚጠጣ በሌለበት በርሃ በ ውሀ ጥም ስትሰቃይ ጋዝ አጠጥተው የገደሉዋት ከደቡብ ክልል ከስልጤ ዞን የመጣቸው እህት ስትሆን
4 ሌሎቹም አንድ (1) ሊትር ውሃ በቀን ለ አስር (10) ሰው እየተሰጣቸው አንዳንድ ብስኩት እያበሉ በርሃብ አለንጋ ተገርፈዋል።
5 የ አምስት (5) ቀናት የእግር ጉዞ ተጉዘው ወደ ግብፅ ድንበር አስዋን በመድረስ ለግብፃውያን የተሸጡ ሲሆን አስራ አምስት(15) ቀን ተጨማሪ ጉዞ ተጉዘው ወደ ሲና ምደረበዳ በመድረስ ከላይ የተጠቀሰውን መከራ አስተናግደዋል።
6 ኪዘህ በኋላ ገንዘብ ከፍሎ የሚያስፈታቸው ሰው በማጣቸው ከሁለት(2) ወር ክስከ አንድ( 1) ዓመት ተሰቃይተዋል።
7 ሽፍቶቹም ገንዘብ እንደማያገኙ ካረጋገጡ በዋላ ኩላሊታችሁን አውጥተን እንሸጣለን በማለት በ አንድ መኪና በመጀመሪያው ዙር ሃያ (20) ወጣቶችን በመውሰድ ሶስቱን (3) ትተው የኤዱ ሲሆን
8 የተወሰዱት ሃያ (20) ወጣቶች የት እንዳሉ አይታወቅም ሶስቱ (3) ግን ከነርሱ በማምለጥ ለሊቱን በሙሉ ሲጓዙ አድረው ወደ ከተማ በመግባት መስጊድ ውስጥ ተጠግተው ያደሩ ሲሆን በመስጊድ ውስጥም ያገኙዋቸው ሼክ እንክብካቤ አድርገውላቸዋል።
9 በሌላ ዙር ወደ እርድ ይዘዋቸው የሚኤዱ ሌላ አስር( 10) ኢትዮጵያውያን በርሃ ውስጥ እየሄዱ ሳለ ምን አድንደተፈጠረ ሳይታወቅ ወረዱ ብለዋቸው በርሃ ላይ ጥለዋቸው መኪናቸውን እያበረሩ ኤዱ በዚህም ግዜ ልጆቹ ወደ ከተማ በምሄድ ከፊተኖቹ ጋር ተቀላቅለዋል የመስጊዱ ሀላፊም ነገሩን ጠይቀው ከተረዱ በዋላ ወደ UNHCR (ዩኤ ኤች ሲአር) በመደውል ችግሩን እንዲሰማ በማድረግ ለጆቹን ከሞት ታድገዋቸዋል ዛሬ በኢትዮጵያውያን ስደተኞች ቢሮ አማከይነት በማገገም ላይ ይገኛሉ።

ከሞት ተርፈው ካይሮ ከገቡት በሀል፡
ስም የትውልድ በታ እድሜ

1 .ሰውአለ ደነቀው ጉጃም ፍኖተሰላም 20
2. በላይ ገ/መስቀል አሪሲ ጼራ 22
3. አትክልት ንጉሴ ትግራይ ኢሮብ 20
4. ዘፈር ብርሃን ትግራይ አዲጉዶም 19
5.ተስፋይ ንጉሴ ትግራይ አምባለጌ 20
6.ሞላ ሰንበታይ ትግራይ አምባለጌ 18
7.ናትናኤል ሞላ ጎንደር አርማጮ 18
8.ኤፍርኤም መከተ ወሎ አማራ ሳይንት 29
9.ሻምበል ማህረግ ወሎ ወልዲያ 20
10. ደመቀ ታሪኩ ጎጃም ማርቆስ 27



Medina Menewera (New Maadi)
Bank El-Ahly Street Building No. 6/3
Cairo, Egypt
Tel 20 251 505 17
Gmail ercie2011@gmail.com
Ethiopian Refugee

1. ሀም[illegible] ኦሮሚያ ጅማ
12. ወንደሰን እንድሪስ ትግራይ
13.ካሊድ ኦሮሚያ ጅማ
14. ሙላት አግማስ ጎጃም በሀር ዳር 18
15.ጌታሁን ሽፈራው ጎንደር እንፍራንስ 24
16 ፅግሬዳ ተሾመ ደቡብ አዋሳ 17
17 ቤዛ ተሾመ ደቡብ አዋሳ 16

በጠቃላይ ባህበሩ ማስተላለፍ የሚፈልግው ነገር:-
1. የበፊቱ በደላሎች የሚፈፅም ሲሆን የአሁኑ ግን ሙሉ በሙሉ በአፊና መሆኑ።
2. የሚታፈኑት ከ ሀገር ቤት ከ ሁመራ እስከ ሱዳን ካርቱም ከተማ ከትራንስፖረት ላይ ሳይቀር በጦር መሳሪያ እያስገደዱ መሆኑ።
3. ይህም በሀገር ያለውን ምንግሰት ጨምሮ አለም አቀፍ መንግስታት እንዲሁም ተቋማት በሙሉ ለዜጎች ጥበቃ እንዲያደርጉ።
4. በተለያየ ቦታ ያሉ ወገኖች በነዚህ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍና መከራ ዓለም አቀፍ ትኩረት እንዲያገኝ በማድረግ ለችግሩ መፍትሔ የሚሰጡ አካላት ላይ ጫና ለመፍጠር የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ በመጨረሻም አሁን ካይሮ የሚገኙት እነዚህ 15 ወንዶችና 2 ሴት ስደተኛ ወገኖች በርሃብና በግርፋት የተጎሳቆለ ሰውነታቸውን እንዲያገግም የበኩችንን ድርሻ እንወጣ ስንል ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የኢትዮጵያ ስደተኞች ማህበር ካይሮ ግብጽ ህዳር 14 ቀን 2012

Ethiopian Refugee Community In Egypt
جمعية اللاجئين الأثيوبيين




Medina Menewera (New Maadi)
Bank El-Ahly Street Building No. 6/3
Cairo, Egypt

Tel 20 251 505 17
GMail ercie2011@gmail.com
Ethiopian Refugee